ግንቦት 7
የፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

Ginbot 7
Movement for Justice, Freedom and Democracy

P.O. Boxes: 4916, 2003EX, Haarlem, The Netherlands; 56281, London, N4 9BH, UK

# እየጠነከረ የመጣው የሕዝብ የተባበሩ እሪታና ሊሰጠው የሚገባ ምላሽ፣

በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የጥናትና ምርምር ኮሚቴ የተዘጋጀ: ሐምሌ 2002

## 1. *መግቢያ፣*

ስለ መተባበር ጠቀሜታ በመዘርዘር ጊዜ ማጥፋት አያስፈልግም። በአገራችን ለዘመናት የተንሰራፋው የግፍ አገዛዝ ያፋፋቸው እና እኛንም በዓለም ፊት እያዋረዱን ያሉት ድህነት፣ ችጋር፣ በሽታና ማይምነት ከመቸውም በላይ ህልውናችንን እመፈታተን ደረጃ ላይ የደረሱት ችግሮቻችንን ለመቋቋም ተባብረን መቆም ባለመቻላችን እንደሆነ አከራካሪ ጉዳይ አይመስለንም። እነዚህን ችግሮች ተባብረን ለማስወገድ የወስድናቸው ተግባራዊ እርምጃዎች ባለመኖራቸው ከዓመት ዓመት እየገዘፉ መጥተው ዛሬ ሊውጡን ደርሰዋል። ከዚህ በፊት በርካታ የመተባበሪያ መልካም አጋጣሚዎችን አባክነናል። ሌላው ሁሉ ቀርቶ ባለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ውስጥ ከመተባባበር ውጭ ዘረኛውና አምባገነኑን ወያኔን በተበታተነ ኃይል ማስቆም እንደማይቻል ሁላችንም አውቀናል። የእብሪተኛው የጥቂቶች አገዛዝ ህልውና የቆመው "በከፋፍለህ ግዛ" መርህ መሰረት መሆኑን በተግባር አይተነዋል:: ለዚህም ነው ባለፉት አስር ዓመታት ኢትዮጵያዊያን በተሰበሰቡበት መድረክ ሁሉ "እባካችሁ ተባብረን እንቁም" የሚሉ የተማፅኖ ንግግሮች መስማት የተለመደ የሆነው። ነገር ግን የመተባበርን ጥቅም መረዳት ብቻውን መተባበርን አይፈጥርም። ሆድን የሚያባቡ "የእንተባበር" ተማፅኖዎች በተግባር እስካልተደገፉ ድረስ ውጤታማ አይሆኑም።

እርግጥ ነው በእነዚህ ዓመታት ከቃላት የዘለሉ የትብብር ሙከራዎች ተደርገዋል። የድርጅቶች ጥምረት ለመፍጠር ተሞክሮ ጥቂት እርምጃዎችን ተጋግዘን የተጓዝንባቸው ጊዜያት ነበሩ። ሆኖም ግን የፈጠርናቸውን ጥምረቶች ዘላቂ እና ውጤታማ ማድረግ ባለመቻላችን እርቀው ሳይሄዱ ተደነቃቅፈው ወድቀዋል። ተጋግዘን ወደፊት ከተጓዝነው ይልቅ ተናቁረን ወደኋላ የምንመለስበት በመብዛቱ ሕዝባችን በብሩህ ተስፋ እና በተስፋ መቁረጥ መካከል እንዲንገዋለል ተፈርዶበታል። ጥምረቶቻችንን ዘላቂና ውጤታማ ማድረግ አልቻልንም። "ምንድነው የጎደልን?" ብለን ራሳችንን በጥብቅ መፈተሽ ይኖርብናል።

ሰሞኑን የመተባበር ጥሪ ከመቼውም በላይ ጎልቶ እየተስተጋባ ነው። ጥሪውን የጎላ ያደረገው ወያኔ ከዚህ ቀደም የማናውቀውን ባህርይ ስላሳየን ወይም የማንጠብቀውን ድርጊት ስለፈፀመ አይደለም። ወያኔ የፈፀመው ምን የማይታወቅና የማይገመት ነገር አለ? የሰሞኑን የመተባበር ጥሪ የቀሰቀሰው ወያኔ በቅርቡ ምርጫ ብሎ በከወነው ትዕይንት በፈጸመው ሸፍጥ የፓርላማውን ወንበር 99.6% በመውሰዱ ምክንያት ነው ብሎ መገመት የተሳሳተ ይመስለናል። ወያኔ ከዚህም የከፋ ነገር ከማድረግ የማይመለስ እኩይ መሆኑን ብዙዎች ኢትዮጵያዊያን እናውቃለን።

P.O. Boxes: 4916, 2003EX, Haarlem, The Netherlands; 56281, London, N4 9BH, UK

አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ያንገበገበው “በምርጫ 2002” አማካይነት ወያኔ ለሁላችንም በጉልህ ያስተላለፈው መልዕክት ነው። ንቀት!!! እጅግ አዋራጅ የሆነ ንቀት!!!! “የምርጫው” ሂደትና የተጠናቀቀበት መንገድ ወያኔ ለሁላችንም ያለውን ንቀት ያለምንም መሸፋፈን በአደባባይ የገለጸበት እብሪት ነው። ከወያኔ ጋር የገጠምነው ትንንቅ ከዴሞክራሲ፣ ከመልካም አስተዳደር፣ ከአገር ጥቅምና ደህንነት በላይ ተሻግሮ ሰው በመሆናችን የእያንዳንዳችን ሰብዓዊ ክብር ለማዋረድ የተቃጣ እብሪት መሆኑን መረዳታችን ነው ሰሞኑ ብዙዎቻችንን በጋራ ቁጣ እንድንተሳሰር ያደረገን። ቻል ብለነውና ትተነው የነበረውን የጋራ ትግል ጥያቄ የቀሰቀሰው ይህ የእያንዳንዳችንን አጥንት ዘለቆ የገባ እንደሰው በክብር ሳይሆን እንደሻገተ አተላ በወያኔ እየተደፋ ያለው ስብዕናችን ነው። “መረረኝ!!! አሁንስ በቃኝ!!! ከዚህ በኋላ ከወገኖቼ ጋር ተባብሬ ይህንን የግል ውርድት ማስቆም ይገባኛል!” የሚል እምነት ነው፣ የዛሬውን የመተባበር ፍላጎት የሚገፋው። ዛሬ ሁላችንም ከሊቅ እስከ ደቂቅ ከደሃ እስከ ሃብታም፣ በአገር ውስጥ ሆነ በስደት ኗሪ በሙሉ፣ ወያኔ ባሰራልን የባርነት እግረ ሙቅ መታሰራችን ፍንትው ብሎ እንዲታየን የተደረገበት ወቅት ነው። ይህ ሃቅ ነው እንግዲህ የመተባበርን ጉዳይ እንደገና ወደ መድረክ ገፍተሮ ያወጣው።

“ምርጫ 2002” ከመተባበር አስፈላጊነት በተጨማሪ ለመተባበር የሚያስቸሉ ሁኔታዎችን አመቻችቷል። የወያኔ እብሪተኛ ድርጊት ወያኔን እንቃወማለን በሚሉ ድርጅቶች መሃል በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የነበሩ ልዩነቶችን ትርጉም አሳጥቷቸዋል። የ2002 ምርጫ “ወያኔ ሊሻሻል ይችላል ወይንስ አይችልም?” “ወያኔን መታገያው ስልት ሰላማዊ ነው ወይንስ የአመጽ?” በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ የነበሩ መናቆሮችን አስቁሟል። ሁሉም በሚያመቸው የትግል ስልት እና እርስ በርስ በተደጋገፈ መንገድ ወያኔ ላይ በጋራ ከመነሳት የተሻለ አማራጭ እንደሌለ አሳይቶናል።

አሁን የቀረን “እንዴት አድርገን ነው ኃይላችንን፣ እውቀታችንን ገንዘባችንን አስተባብረን የወያኔን እድሜ የምናሳጠረው?” የሚለው አጀንዳ ብቻ ነው። በወያኔ መረገጥ የተማረረው ሕዝብም ሆነ የተቃዋሚ ድርጅቶች ካለፉ የመተባበር ተመክሮዎች በመነሳት “ጊዜው የሚጠይቅውን ጥብቅ ትብብር ለማሳካት እንዴት እንችላለን?” የሚል ጥያቄ ማንሳት ጀምሯል። የወደፊቱ ትብብር እንዳለፉት ትብብሮች የታለመለትን ግብ ሳይመታ እንዳይቀር ምን መደረግ ይኖርበታል በማለት መጨነቅ ጀምረዋል። የዚህ ጽሁፍ ዓላማ እነዚህን ጥያቄዎችና ጭንቀቶች ግምት ውስጥ ያስገባና በተወሰነ ደረጃ ለውይይት መነሻ የሚሆን መንደርደሪያ ሃሳብ ለማቅረብ ነው።

እንደ ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ እምነት፣ በደንብ ካሰብንበት፣ ከተዘጋጀንበትና ከደከምበነት የታለመለትን ግብ ሳይመታ የማይቆም በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚገኙ በመቶዎች የሚቆጠሩ የተለያዩ ድርጅቶቸና በአስር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በአንድ ዓላማ ስር የሚተባበሩበት የፀረ-ወያኔ የተባበረ እንቅስቃሴ መፍጠር ይቻላል። ይህን የተቀደሰ ሃሳብ ለማሳካት ግን ብዙ ጥያቄዎችን አንስተን በአጥጋቢ ሁኔታ መመለስ ይጠበቅብናል። ይህ ጽሁፍ ስለመተባበርና ስለድርጅቶች ጥምረት ዋና ዋና ነጥቦችን ካነሳና የዓለም ዓቀፍ ልምድንም ከዳሰሰ በኋላ ወደአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በመመለስ እስካሁን **ምን ተሰራ፣ ምን ጎደለ ? ወደፊትስ ምን ማድረግ**

<u>ይጠበቅብናል?  በሚሉ ነጥቦች ላይ ያተኩራል።</u> የያዝነው ርዕስ ሰፊና ሞጋች ቢሆንም በጥቂት ገፆች ለመወሰን መጣራችንን ትገነዘቡልናላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

## 2. መተባበር መቻል ጥበብ ነው፣

ከላይ እንደተጠቀሰው ስለመተባበር ጥቅም ማውራት እምብዛም ፋይዳ የለውም፤ የታወቀ ነው። ይልቁንስ "ሰዎች የመተባበርን ጥቅም እያወቁ የማይተባበሩት ለምንድነው?" የሚለውን "እንቆቅልሽ" መፍታት እጅግ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ሰዎች መተባበር የማይፈልጉባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። መተባበር ፈልገው እያለም ከመተባበር የሚያግዷቸው ሌሎች በርካታ ምክንያቶች አሉ። ሶስት ዋና ዋና ችግሮችን እናንሳ፣

### 2.1. የማስተባበር ችግር፣

ተባብሮ ለመሥራት ፍላጎትም ዝግጁነትም ኖሮ እያለ በአስተባባሪ እጦት ምክንያት ትብብር ተግባራዊ ላይሆን ይችላል። እዚህ ላይ "አስተባባሪ" ሲባል ሰውንም ተቋምንም ይመለከታል። <u>የኅብረት ሥራ ህግ፣ ሥርዓትና ድርጅት ይጠይቃል። በጋራ የሚሠራ ሥራ ማን ምን እንደሚሠራ እና ሥራው መሠራቱ የሚቆጣጠረው ማን እንደሆነ ግልጽ ተደርጎ ካልተጀመረ "እንተባበር" ስለተባለ ብቻ ኅብረት አይመጣም</u>። በስፖርት - ለምሳሌ - የቡድን አባላት በጨዋታው ዓይነትና ህግ መስማማት አለባቸው፤ ቀጥሎ ደግሞ ኃላፊነቶችን መከፋፈል ይኖርባቸዋል። ለእግር ኳስ የተገናባ ቡድን ለመረብ ኳስ አይሆንም። ግልጽ የሆነ ዓላማ፣ ደንብና መዋቅር የመኖሩ አስፈላጊነት በሁሉም የኅበረት ሥራዎች ውስጥ የማይቀር ነገር ነው። በዚህ ረገድ በስፓርትም፣ በእድርም፣ በፓለቲካ ፓርቲዎችም ዘንድ ያለው ችግር ተመሳሳይ ነው።

ይህ ችግር ለመፍታት የሚያስፈለጉ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች አመራርና /leadership/ እና ማኔጅመንት ናቸው። በዚህ ረገድ ባህል እጅግ ከፍ ያለ ሚና ያለው፤ በአጭር ጊዜ ለመቀየር የሚያስቸግር ነገር ነው። በባህል ጉዳይ ወደ ኋላ እንመለስበታለን።

### 2.2. የመተማመን እጥረት፣

የኅብረት ሥራዎች ትልቁ ችግር አብረው ለመቆም በተስማሙ አባላትና አካላት መካከል ያለው የመተማመን ደረጃ ለኅብረቱ ፍሬያማ ውጤት ወሳኝ የመሆኑ ክፋት ነው። በተወሰነ መጠን ቢሆንም እንኳን በገበያ (በኢኮኖሚ) ሳይተማመኑ መተባበር ይቻላል። **በፓለቲካ ውስጥ ግን ሳይተማመኑ ለመተባበር ያለው እድል እጅግ የጠበበ ነው። "ያዛልቀኝ ይሆን?" ወይስ "ይከደኝ ይሆን?" የሚለው ጥርጣሬ በጋራ ሥራ ላይ ጊዜ፣ እውቀትና ሃብት ላለማፍሰስ ሰበብ ሊሆን ይችላል።** የመተማመንን እጥረት ለማስወገድ የሚረዳ አስተማማኝ መፍትሄ ባይኖርም የሚከተሉት ነጥቦች ጠቃሚ ናቸው ተብሎ ይገመታል።

2.2.1. በተቻለ መጠን ሁሉም ተሳታፊዎች የኅብረቱ ተጠቃሚዎች ማድረግ፤

2.2.2. ለአባል ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች ስምና፣ ክብር ከፍ ያለ ዋጋ መስጠት (ግለሰቦችም ተቋማትም የገነቡትን መልካም ስምና ዝና /reputation/ እንዳያጡ ለውሎች ታማኝ ይሆናሉ ተብሎ ይገመታል)፤

2.2.3. ስምምነቶች ሁሉ በተቻለ መጠን በጽሁፍ እንዲሆኑ ማድረግ፤

2.2.4. መሪዎችን ውል የማፍረስ አቅም ማሳጣት። ውል በቀላሉ እንዳይፈርስ በመተዳደሪያ ማጥበቅ፤ እና

2.2.5. ትብብርን በትናንንሽና ለማስፈጸም ቀላል በሆኑ ጉዳዮች ጀምሮ ደረጃ በደረጃ ማሳደግ።

## 2.3. በግል ኪሳራና እና በጋራ ጥቅም መካከል ያለው ተቃርኖ፣

ከኅብረት ሥራ የጋራ ጥቅም ቢገኝም በግል የሚያመጣው ጉዳትም አለ። እያንዳንዱ ተሳታፊ ከጋራ ጥቅም ለመጠቀም፤ ከግል ጉዳት ደግሞ ለመሸሽ ቢጥር የሚገርም ሊሆን አይገባም። ይህ የተለመደ የሰው ልጅ ስሌት ነው። እያንዳንዱ ሰው ጥቅምና ጉዳቱም ማመዛዘኑ ተፈጥሯዊ ነው። ለኅብረት ሥራ ይኸ ተቃርኖ ችግር የሚሆነው የሥራው ውጤት በልፋት መጠን ማከፋፈል በማይቻልበት ወቅት ነው። ብዙዎቹ የኅብረት ሥራ ውጤቶች ጭራሹኑ የማይከፋፈሉ ናቸው። በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ ጭምት ነኝ ባይ ራሱ እያሸሸ በድካም የተገኘውን ውጤት ለመካፈል ግን ቀድሞ ተሰላፊ ይሆናል።

ይህ ችግር ውብስብስ በመሆኑ ቀላል መፍትሄ የለውም። የነፃነት ታጋዮች ከግል የጥቅም ፍላጎት እርቀው ለዓላማ የመቆምን መንፈሳዊ ጽናት ሲኖራቸው ብቻ ነው፣ ይህን ምድራዊ ፈተናን መቋቋም የሚችሉት። የርዕዮት-ዓለም ጥቅሙ እዚህ ጋ ነው። ይህንን ፈተና ሊቋቋም የሚችል ምን ዓይነት ርዕዮተ ዓለም ሊኖረን ይገባል የሚለው ጉዳይ በጥልቀት ሊታሰብበት ይገባል።

ለሁሉም የትብብር ችግሮች መፍትሄ ማመንጨት ባንችልም ቢያንስ የችግሩን ጥልቀት አውቀን መነሳታችን ቀድሞ በገባንባቸው ጉድጓዶች ውስጥ ደግመን እንዳንገባ ያግዙናል።

# 3. የድርጅቶች ጥምረትም (coalition) ደግሞ ራሱን የቻለ ሌላ ጥበብ ነው፣

ጥምረት የየራሳቸው ዓላማና ግብ ያላቸው የተለያዩ ቡድኖች በሚግባቡባቸው ጉዳዮች ላይ የሚሠሯቸውን ተግባራት ለማስተባበር የቆመ የቡድኖች ኅብረት ነው።

የቡድኖች ኅብረት የሚፈልገው በአንድ ቡድን ብቻ ሊሰሩ የማይችሉ ቢሰሩም ጥራታቸውና ተፈላጊነታቸው የሚጓደል ሥራዎች ስላሉ ነው። ስለሆነም ስለድርጅቶች ጥምረት ከመታሰቡ በፊት

ጥምረቱ ያመጣዋል ተብሎ የሚገመተው ውጤት በአንድ ድርጅት ብቻ መምጣት የማይችል መሆኑን፤ ቢመጣም ተቀባይነቱ አነስተኛ መሆኑ በሁሉም ተጣማሪ ድርጅቶች ዘንድ የጋራ ግንዛቤ ሲኖር ነው።

የድርጅቶች መጣመር በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት።

- ጥምረት ኃይልን ይገነባል፤ "ድር ቢያብር አንበሳን ያስር" እንዲሉ በየግላቸው ደካማ የሆኑ ቡድኖች ሲተጋገዙ ይጠነክራሉ። ይህ ምናልባትም ከሁሉም በላይ ግልጽ የሆነ የጥምረት ጠቀሜታ ይመስለናል።
- የድርጅቶች መጣመር ደጋፊን ያበዛል። ተጣማሪ ድርጅቶች በየግላቸው ያልማረኩት የኅብረተሰብ ክፍል በጥምረታቸው ሊማረክ ይችላል። በዚህም ምክንያት የድርጅቶች ጥምረት ተጣማሪዎቹ ድርጅቶች በግልም በጋራም ያላቸው ሕዝባዊ ተቀባይነት /legitimacy/ ከቀድሞው እጅጉን የላቀ እንዲሆን ያደርጋል።
- ጥምረት በጥሩ ማኔጅመንት ከታገዘ ጊዜን፣ ሰውን፣ ገንዘብን፣ እውቀትን፣ መረጃን፣ እና ኔትዎርክን በተሻለ ስልጠት /efficiency/ ለመጠቀም ያስችላል።
- በጥምረት ውስጥ ያሉ ድርጅቶች ለሁኔታዎችና ክስተቶች የሚሰጡት ትርጉም እንደየድርጅቶቻቸው እይታ የተለያየ በመሆኑ አንድን ጉዳይ ከተለያዩ አቅጫዎች የመመልከት እድልን ያሰፋል።

የእነዚህና መሰል ጠቀሜታዎች መኖር ነው ድርጅቶች በየግላቸው ተሯሩጠው ከሚያመጡት ውጤት ድምር በላይ በጋራ ሲሆኑ ይመጣል የሚባለው። እንደ አገራችን ያለ በበርካታ ችግሮች ለተተበተበች አገር የጥምረት ጠቀሜታ ከዚህም በላይ ነው። ሎሚና ብርቱካንን መደመር እንደማይቻል ሁሉ የአንዱ ፓርቲ ድል ከሌላው ፓርቲ ድል ጋር የማይደማመሩ ሁለት ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ስለሆነም የጋራ የሆነ ነገር (ለምሳሌ ስጥሪስ ጭማቂ) ላይ መስማማት ያስፈልጋል። ጥምረት ይህንን ወሳኝ የሆነውን ስምምነት መፍጠሪያ መድረክ ሆኖ ያገለግላል።

ይሁን እንጂ አጓጊ ጠቀሜታዎችን በማየት የድርጅቶች ጥምረት በችኮላ የሚደረግ መሆን የለበትም። ጥምረት የታወቁ ጉዳቶችም አሉት። ከሁሉ አስቀድሞ ጥምረት ድርጅቶች ከለመዱት አሰራር ስለሚያወጣቸው ውዥንብርና መደነጋገር የሚፈጥር መሆኑ ታውቆ ቅድሚያ ዝግጅት ሊደረግበት ይገባል። በዚህ ረገድ በቂ የሆነ ቅድመ ዝግጅት ካልተደረገለት የመጣመር ሙከራ ራሱ የቅራኔ ምንጭ ሊሆን ይችላል። በጠንካራ መሰረት ላይ ያልተገነባን ጥምረት ማቆየት ራሱን የቻለ ሥራ ይሆንና ሌሎች ሥራዎችን ያዘናጋል። ተጣምረው በተፋለሱ ድርጅቶች መካከል የሚኖረው ቅራኔ ከመጣመራቸው በፊት ከነበረው የባሰ ሊሆን ይችላል። ይህ በቅርብ ጊዜ ታሪካችን ውስጥ ያየነው ጉዳይ ነው። የጥምረቱ ድርጅታዊ መዋቅር በጥንቃቄ ካልተዘጋጀ ሥራዎችን በማፋጠን ፋንታ ሊያጓትት፤ ግብዓቶችን ቆጥቦ በመጠቀም ፋንታ ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል። በሁሉም የጋራ ሥራዎች ላይ ያለ "ልፋት ለሱ፤ ጥቅም የጋራ" ዓይነቱ የብልጣ ብልጥነት መርሆ በድርጅቶችም ላይ ያለ መሆኑን

መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም በጥምረት ውስጥ ያሉት ድርጅቶች ሁሉ እኩል ከልባቸው የአቅማቸውን ያህል ይሳተፋሉ ብሎ መነሳት የዋህነት ሊሆን ይችላል። ሁሉም ድርጅቶች እኩል ስለማይሳተፉ የአንዳንድ ድርጅቶች ሚና ከሌሎቹ ከፍ ሊል የሚችል መሆኑ ከመነሻው ሊታወቅ ይገባል።

ስለሆነም ጥምረት በሚገባ ተጠንቶ ደረጃ በደረጃ የሚደራጅ እንጂ ለመተባበር ወይም "አብረን ነን" ለማለት ብቻ የሚፈጠር ተቋም አለመሆኑ መረዳት እጅግ ጠቃሚ ነገር ነው ብለን እናምናለን:: ።

## 3.1. የጥምረት ተግዳሮቶች፣

የጋራ ዓላማ ያላቸው ድርጅቶች በመተጋገዝ ፋንታ ሲጎነታተሉ ማየት አዲስ ነገር አይደለም። ሸሪኮች ሊሆኑ ይገቡ የነበሩ ድርጅቶች ባላንጣዎች ሲሆኑ ጉዳቱ ጥልቅና ሰፊ ነው። ስለሆነም ለጥምረት የሚደረገው ጉዞ መጀመር ያለበት ባላንጣነትን ወይም መጎነታተልን በማስቀረት ነው። የወዳጅ-ባላንጣ በብዙ ምክንያቶች ሊፈጠር ይችላል፤ ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

1. ግቦቻችን የተለያዩ ናቸው ከሚል የተሳሳተ ግንዛቤ፤
2. የራስን ድርጅት "ግዛት" የመጠበቅ ፍላጎት - ሌሎች ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ድርጅቶች ደጋፊዎቼን ይወስዱብኛል የሚለው ስጋት፤
3. በራስ ድርጅት ውስጥ የተያዘ ሥልጣን በጥምረቱ ውስጥ አይገኝ ይሆናል የሚል ሥጋት፤ እና
4. በመሪዎች የግል የስብዕና ችግር - አንዳንድ የፓለቲካ መሪዎች እነሱ የማይመሩት ድርጅት እንዲኖር ፍላጎታቸው አይደለም።

በወዳጅ ድርጅቶች መካከል ያለው ባላንጣነት ለማስወገድ የስኬታማ ተግባቦት (effective communication) ክህሎቶችን ማዳበር ግድ ይላል። ከስኬታማ ተግባቦት ክህሎት ዋነኛው ደግሞ ከልብ ማዳመጥ መቻል ነው። ድርጅቶች በባላንጣነት የሚያዩዋቸውን ወዳጆቻቸውን ከልብ ማዳመጥን መልመድ ይኖርባቸዋል። ከልብ ለማዳመጥ ደግሞ በሌላኛው ድርጅት ዓላማዎች ላይ ፍላጎት ማሳደር ግድ ይላል። ግድየለሽ ተኩኖ ከልብ ማዳመጥ አይቻልም። ሌላው የመደራደር ፈቃደኝነት ነው። ድርድር ደግሞ በማግኘት ስሜት ብቻ አይደረግም። በድርድር አንድን ነገር ለማግኘት ሌላ ነገር ማጣትን ሊኖር እንደሚችል ማመን ያስፈልጋል። መልካም ድርድር ከመስጠትና መቀበል አልፎ የተሻለ ጎዳና ለማግኘት መጣርን ያካትታል። "ይህ ያንተ መንገድ አይደለም፤ የኔ መንገድም አይደለም። ለሁላታችንም የተሻለ ጎዳና ነው" ዓይነት ውጤት ነው የተሳካ የድርድር ውጤት የሚባለው። የምናልመው ጥምረት እንዲህ ዓይነቱ የተሻለ ጎዳና ላይ የሚያስቀምጠን ሊሆን ይገባል።

## 3.2. የጥምረት ዓይነቶች፣

የጥምረት ዓይነቶች በርካታ ሲሆኑ ሶስቱን ከዚህ በታች እናያለን።

1. ድጋፍ ሰጭነት/Endorsement/
   - ድርጅቶች ድጋፍ ለመስጣጠት የሚያደርጉት ልል ጥምረት ነው።
   - ከድጋፍ ያለፈ እምብዛም የሚያደርጉት የለም።
   - ከመግባቢያ ሰነድ ያለፈ ስምምነትም ላይኖራቸው ይችላል።
2. ዝምድና /ተዛማጅ/Associate/
   - አባል ድርጅቶች ህያው የሆነ የጋራ ተሳትፎ ያደርጋል።
   - ሥራዎች ቢቀናጁም ውሳኔዎች ግን የግል ናቸው።
   - በዚህ ደረጃ ላይ የጥምረቱን ሥራዎች የሚያስተባብር ከአባል ድርጅቶች የተወጣጣ አካል እና ይህ አካል የሚተዳደርበት ቢጋር /terms of refernce/ ይኖረዋል።
3. ሽርክና /Partner/
   - ውሳኔዎች የጋራ ናቸው። የጥምረቱ ውሳኔዎች በአባል ድርጅቶች ውሳኔ ላይ የበላይነት አላቸው።
   - ሽርክናው ራሱን የቻለ ድርጅት ሆኖ በመቋቋም የድርጅቶች ጃንጥላ ሆኖ፤ የራሱን መዋቅር ዘርግቶ ይንቀሳቀሳል። አንዳንድ የሥራ ዘርፎች (ለምሳሌ ራስን የመከላከል ሥራ፣ የውጭ ግኑኝነት፣ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች) ሙሉ በሙሉ ለሽርክናው ሊተው ይችላሉ።

የትኛው የጥምረት ዓይነት ይሻላል የሚለው ጥያቄ የሚወሰነው ለሚከተሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች በሚሰጥ ምላሽ ነው።

ሀ) አባል ድርጅቶች ምን እንዲያደርጉ ነው የሚጠየቁት?
ለ) እያንዳንዱ አባል ድርጅት ከጥምረቱ ምን እና እንዴት ይጠቀማል?
ሐ) የእያንዳንዱ አባል ድርጅትና አቅምና ዝግጁነት ምን ያህል ነው?

ሁሉም ድርጅቶች በእኩል ደረጃ ላይ ሊገኙ ስለማይችሉ ሶስቱንም የጥምረት ዓይነቶች እንደሁኔታው የምናስተናግድበትን ብልሃት መፍጠር ይኖርብናል።

ግንቦት 7
የፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
Ginbot 7
Movement for Justice, Freedom and Democracy

P.O. Boxes: 4916, 2003EX, Haarlem, The Netherlands; 56281, London, N4 9BH, UK

## 4. በሌሎች አገራት ከነበሩ ኅብረቶችና ጥምረቶች ምን እንማራለን?

በታሪክ ውስጥ የሚጠቀሱ አንዳንድ ትብብሮችና ጥምረቶች ለማመን የሚቸግሩ ውጤቶችን አስገኝተዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች በመሣሪያ ሊገኝ ከሚችል ድል በላይ በተቃዋሚ ድርጅቶች ተባብሮ መቆም ብቻ ሊገኝ ይችላል። ለምሳሌ ያህል የምከተሉትን ማንሳት ይቻላል።

4.1. በእንግሊዝ በ1688-1689፤ በስዊድን በ1909 በፍላጎትም በርዕዮተ-ዓለምም የማይቀራረቡ የመሳፍንትና የቡርዧ ቡድኖች ተደራድረው በፈረንሳይ የፈነዳውን ዓይነት ማኅበራዊ ነውጥ ሳያስፈልግ ለሥርዓት ለውጥ በቅተዋል።

4.2. በኮሎሚቢያ 1957-1958 ተቃዋሚ ፓርቲዎች ኅብረት ፈጥረው በመፈርጠማቸው የተደናገጠው በሥልጣን ላይ የነበረውን ቡድን ግማሽ የመንግሥት ሥልጣኑን በመልቀቅ የፕሬዚዳንትነት ሥልጣን ከተቃዋሚዎች ኅብረት ጋር በፈረቃ ሊለዋጥ ተስማምቷል።

4.3. በተመሳሳይ ሁኔታም በቬንዙዌላ በ1958 ተቃዋሚዎች የፈጠሩት ሰፊ መሠረት ያለው ኅብረት ሥልጣን ያለውን ፓርቲ አርበድብዶ አነስተኛ በሆነ መስዋትነት ሥልጣኑን እንዲለቅ ማድረግ ችለዋል።

4.4. በ1989 የፓላንድ የሙያ ማኅበራትና ሌሎች የፓለቲካና ማኅበራዊ ስብስቦች በሙሉ "ከሶሊዳሪቲ" ጎን በመቆማቸው ኮሚኒስት ፓርቲው ራሱን ለማዳን እንዲደራደር ማስገደድ ችለዋል። በተመሳሳይ ጊዜ ተመሳሳይ ነገር በቼኮዝላቫኪያ ውስጥም ተከስቷል።

4.5. በ1994 በደቡብ አፍሪካ በኤኤንሲ ግንባር ቀደም መሪነት የተካሄዱ ጥምረቶችና ድርድሮች እጅግ ውስብስብና አስደናቂ ጥበብ የተሞላባቸበው ነበሩ። በተለይም እነዚህን ድርድሮች በዝርዝር ማጥናት እኛ ለምንገኝበት ሁኔታ ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው ብለን እናምናለን።

ከላይ የተዘረዘሩት እና የመሳሰሉ ክስተቶች በጣም አልፎ አልፎ ብቻ የሚያጋጥሙ ብርቅየዎች ከመሆናቸም በላይ እያንዳንዱ ክስተት ከበርካታ ዓለም ዓቀፍ እና አገር ዓቀፍ ሁኔታዎች የተሳሰሩ ነበሩ። ስለሆነም አንዳቸውንም መድገም አይቻል ይሆናል፤ ሆኖም ግን እያንዳንዱ ምሳሌ የተለያዩ ፍላጎቶች ያላቸው አካላት የአብሮ መቆም መቻላቸውን እና አብሮ መቆም ያለውን የለውጥ ጉልበት አጉልተው ያሳያሉ።

## 5. ከራሳችን ያልተሳኩ የትብብርና ጥምረት ሙከራዎች ምን እንማራለን?

### 5.1. እንደ መንደርደሪያ፣

በአገራችን ታሪክ በፖለቲካ መስኩ የተደረጉ ብዙ የመተባበር ሙከራዎች አሉ። እነዚህን ሙከራዎች በሶስት አይነት መክፈል ይቻላል።

የመጀመሪያው፣ አንድ ተጽእኖ ማድረግ በሚችል ድርጅት ዙሪያ የተወሰነ የራሳቸው ነፃነት ያላቸው ነገር ግን አቅማቸው ደካማ የሆኑ ድርጅቶች የፈጠሩት ትብብር ነው።

ሁለተኛው፣ አቅማቸው ተመጣጣኝ የሆኑና ተመጣጣኝ ያልሆኑ ነገር ግን አንዳቸው በሌላው ላይ ተጽእኖ ማድረግ የማይችሉ የነፃ ድርጅቶች ትብብር ነው።

ሶስተኛው፣ አንድ ጠንካራ ድርጅት ምንም ዓይነት ነፃነት የሌላቸውን ድርጅቶች በማሰባሰብ ፈጠርኩ የሚለው ትብብር ነው።

ለመጀመሪያው ዓይነት ትብብር፣ በደርግ/ሰደድና በሌሎቹ ኢማሌድህ በተሰኘው ስብስብ ውስጥ አባል በነበሩት ድርጅቶች መሃል ተፈጥሮ የነበረው ኅብረት ምሳሌ መሆን ይችላል።

ለሁለተኛው አይነት ትብብር፣ ምሳሌ መሆን የሚችሉት ወያኔ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ወያኔን ለመቃወም ተቋቁመው የነበሩትን ትብብሮች ይመለከታል። የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ሕብረት (ኢተፖድሕ)፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት (ኢዲኃሕ)፣ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ (ቅንጅት)፣ ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ በሚል ስያሜ የሚታወቁት ትብብሮች የሁለተኛው ዓይነት ትብብር አገራዊ ምሳሌዎች ናቸው።

ሶስተኛው አይነት ትብብር፣ በስሙ ካልሆነ በስተቀር በመሠረቱ ትብብር አይደልም። ለእንዲህ አይነቱ “ትብብር” ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በወያኔ የሚዘወረው ኢህአዴግ ነው።

እነዚህ የትብብር ሙከራዎች በሙሉ በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ሊሳኩ አልቻሉም። የወያኔው ኢህአዴግ ዓይነቱ ትብብር መጀመሪያውኑ ሲታሰብ ወያኔ የራሱን ጡንቻ ካፈረጠመ በኋላ ለረጅም ግዜ ታጥሮ ከኖረበት ትግራይና የትግራይ ሪፐብሊክ ምስረታ ህልሙን በጉያው ሸጉጦ ወደ መሃል አገር ለመገስገስ ያለውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ሲል እራሱ ጠፍጠፎ ከፈጠራቸው ድርጅቶች ጋር የተመሰረተ በመሆኑ ትብብር ከሚለው ጎራ መመደቡ ተገቢ አይደለም ይባል ይሆናል፤ ይህ አባባል እውነት ነው። ይሁን እንጂ በኅብረት ስም እንደምን ያህል ነውር እና ወንጀል መፈጸም እንደሚቻል ኢህአዴግ ምሳሌ በመሆኑ እዚህ ላይ መጠቀሱ ተገቢ ነው እንላለን።

የወያኔ የባህል ዝንባሌ ሃገር በቀል በመሆኑ ሌሎችም ድርጅቶች ቢሆኑም ለብቻቸው ስልጣን መያዝ ባይችሉ፣ አቅሙና ሁኔታው እስከፈቀደላቸው ድረስ ነፃና እኩያቸው ከሆኑ ድርጅቶች ጋር እውነተኛ ትብብር ከማድረግ ይልቅ በድብቅ ራሳቸው ከፈለፈሏቸው ወይም ከሚቆጣጠሯቸው ድርጅቶች ጋር ትብብር አደረግን ማለት የሚመቻቸው ለመሆኑ ጠቋሚ ነው። ትብብር የሚደረገው ልዩነት ባላቸው ኃይሎች መሃከል ያለውን ቅራኔ አስወግዶ ለሁሉም የሚመች መንገድ ለመፈለግ መሆን ሲገባው የተለጣፊ ድርጅቶች “ትብብር” በመፍጠር የራስን አጀንዳ በሌሎች ችከሻ ማስፈፀም በመጨረሻ ለብልጣብልጡ ድርጅት ሳይቀር ችግር እንደሚፈጥር ከወያኔ የጥፋት ታሪክ መማር ተገቢ ነው። “ኢህአዴግ” እያለ ወያኔ የሚጠራውን የወሮበሎች ተቋምን በትብብር ምሳሌነቱ ማንሳት ተገቢ

የመሰለንም በተመሳሳይ መንገድ ትብብርን ለአንድ ድርጅት ጠባብ ዓላማ የማዋል ዝንባሌ ከወያኔም ውጭ ይኖራል ብለን ስለምናምን ነው ።

የኢማሌድህ ትብብር በሰደድ አሸናፊነት መጠናቀቁ ብዙም ሊገርመን አይገባም። የትብብሩ ዓላማ የመድበለ ፓርቲ የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር ሳይሆን የሠራተኛውና የአርሶ አደሩን ጥቅም የሚያስከብር አንድ ሶሻሊስት ፓርቲ መመስረት ስለነበር ሰደድ ሁሉንም ጨፍለቆ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) ብቸኛ ጌታ ሆኗል። በዚህ ምሳሌም ውስጥም ቢሆን ጠቃሚ ትምህርት የለም ማለት አይደልም። ሥርዓቱ የሚያዘው በአንድ አገር አንድ ፓርቲ ብቻ እንዲኖር ቢሆንም በጋራ ለዚህ ፓርቲ መመስረት መሰባብ የጀመሩ ድርጅቶች እርስ በርስ ሳይባሉ ተከባብረወና ተስማምተው ራሳቸውን አንድ ማድረግ አለመቻላቸው ራሱ የሚሰጠን ትምህርት አለ። እንዲህ አይነቱ መጠፋፋት የርዕዮት-ዓለም ልዩነት በሌላቸው ድርጅቶች መካከል ሊፈጸም ከቻለ የርዕዮት-ዓለም ልዩነት አለን በሚሉና የየራሳቸውን አደረጃጀት ይዘው በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች መካከል በመከባበርና በስምምነት ላይ የተመሰረትተ የትግል ኅብረት ለመፍጠር የሚኖረውን ችግር ጥልቀት መረዳት አያስቸግርም። **ይህ እውነታ የሚያሳየን በኢትዮጵያ ውስጥ በጋራ ለመስራት የሚደረጉ ጥረቶች እንዲሳኩ የድርጅቶች የዓላማና የፖሊሲዎች ተመሳሳይነት ብቻው በቂ እንደማይሆን ነው።**

ወያኔ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላም የተደረጉ በርካታ ተባብሮ የመስራት ሙከራዎች መሰናከል ምክንያቶች እንደ ትብብሮቹ ሁሉ በርካታ ናቸው። ችግራችን ግን በዋንኛነት ስለ ወያኔ ምንነትና ማነነት፣ ወይም በተለያዩ ፖሊሲዎች ላይ ካለን ልዩነት የመጣ አይደለም። ኢማሌድህ ውስጥ ሰደድ ሁሉንም ውጦ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምን ብቸኛ አዛዥ እንዳደረገ ሁሉ፤ ወያኔም ተለጣፊዎቹን አሰባስቦ የመለስ ዜናዊ የግል ተላላኪ አድርጎ እንዳሰማራ ሁሉ፤ ግላዊና ማኅበራዊ ስነልቦናችን እንዲሁም ባህላችን ሁሉንም ጠቅልሎ ለመቆጣጠር ፍላጎት ያላቸው የፖለቲካ ሰዎችን የሚያመርት መሆኑ ከወያኔ በኋላ ለተሞከሩት ትብብሮች ውድቀት ዋነኛው ምክንያት ነው። የፖለቲካ ሰዎች ለላቀ አገራዊና ሕዝባዊ ጠቀሜታ ሲሉ እኔ ብቻ ያልኩት ካልሆነ፣ የኔ ድርጅት ይህንን ስልጣን በትብብሩ ውስጥ ካልተሰጠው፣ የኔ ድርጅት የተለየ ጠቀሜታ ካላገኘ በሚሉ ድብቅ ፍላጎቶች የሚነሱ ተግባራትን መቆጣጠር ባለመቻላቸው እነዚህ ትብብሮች ለመፍረስ ችለዋል። ምክንያቶቹ ግን እነዚህ ብቻ ናቸው ግን ማለት አይደለም።

ከወያኔ ስልጣን ላይ መውጣት በኋላ ለተሞከሩ የትብብር ምስረታዎች መክሸፍ ኋላቀር አመለካከታችን ያሳደረውን ተጽዕኖ የሚያሳዩ ሌሎችን በማስረጃ የተደገፉ በርካታ ምሳሌዎች ማቅረብ ይቻላል። ሆኖም ክርክራችንን በማስረጃ ብናስደግፍም እንኳን በግለሰቦችና በድርጅቶች ላይ የተሰንዘረ ጥቃት መስሎ ስለሚታይ ሊፈጠር ይገባል ብለን ለምናልመው አዲስ የትብብር ጅማሮ እንቅፋት ይሆናል በሚል ስጋት በዝርዝር ልንገባበት አንሻም። ስለሆነም እገሌን ከእገሌ ባልለየ ባለዩ መልኩ ጉድለቶቻችንን ለይተን በማየት ለወደፊቱ የሚሆን ትምህርት ለመቅሰም በሚያበቃን መጠን ብቻ ጥቂት ምሳሌዎችን እናነሳለን።

“ትብብርን” ተጠቅሞ የራስን ድርጅትና ሌሎችን በእኩልነትና በመግባባት ለማስተናገድ ፈቃደኛነቱ ያልታየባቸው ሁኔታዎች ለትብብር መፍረስ ምክንያት ሆነዋል። ትብብር የሚል ቃል ተጠቅሞ ሊተባበሩ ፍላጎቱን ባሳዩ ኃይሎች መካከል ከዚህ ቀደም የነበረ ግጭትና መቃቃር መልሶ ሕይወት እንዲዘራ በማድርግ በትብብሩ ውስጥ የተካተቱ ኃይሎችን በቂምና በጥላቻ ዓይን ማየት፣ የግለሰቦችንና የድርጅቶችን ስም በመርዘኛ ወሬና አሉባልታ ማጥፋት ሌላው ችግር ነው።

ትብብርና ቂም፣ ትብብርና ጥላቻ፣ ትብብርና ንቀት፣ ትብብርና ሸፍጥ፣ ትብብርና ግለኛነት አንድ ላይ ሊሄዱ አይችሉም። ያለን ምርጫ ከሁለት አንድ ብቻ ነው። እነዚህ ሁለት ምርጫዎች ወይ ቂማችንን፣ በቀለኛነታችንን ጥላቻችንን፣ ንቀታችንን፣ ግለኛነታችንን ታቅፈን ሁላችንም በተናጠልና በጋራ መለስ ዜናዊን የመሰለ ፀረ-ኢትዮጵያ ዘረኛ አዋርዶና ቀጥቅጦ እንዲገዛን እና በብዙ መስዋዕትነት ቀድምቶቻችን ያኖሯትን ሃገር እንዳሻው እንዲዘርፍና እንዲያፈርስ መፍቀድ፣ አልያም ለመተባበር እንቅፋት የሆኑትን ባህላዊና ስነልቦናዊ እንከኖች ከውስጣችን መጥርግና ለነፃነት፣ ለፍትህ፣ ለእኩልነትና ለአንድነት በጋራ መቆም ናቸው።

ያነሳነው ችግር ስር የሰደደ የባህል ችግር ነውና “እባካችሁ እናጥፋው” በሚል ሰበካ ብቻ ሊጠፋ እንደማይችል እናውቃለን። ነገር ግን ችግሩ እንዳለ እስካወቅን፣ በተለይ ችግሩ ሁላችንም ይመለከታል ብለን ለመፍትሄ ከጣርን እድሉን ካገኙ አገርን የመምራት ብቃት እንዳላቸው ለሚናገሩ የፖለቲካ መሪዎች የሚሳን ሊሆን አይገባውም። ሆኖም ግን ይህንን ችግር ለመቅረፍ ራሳቸንን እንመርምር ከሚል ተማጽኖ በላይ ተሻግረን ያለፉ ትብብሮችን ያሰናከሉ ችግሮች ደግመው እንዳይከሰቱ መዋቅራዊና መርሃዊ መከላከያዎችን ማስቀመጥ ይኖርብናል። ይህን ለማድረግም ሁኔታዎች ከመቼውም በላይ የተመቻቹ ናቸው።

አዲሱ የፖለቲካ ግንዛቤ፣ በተለይ በዋንኛው የአገሪቱ የፖለቲካ ችግር ላይ ያለው ግንዛቤ ከተለያዩ ብዥታዎች ጠርቶ አንድ መስመር ይዟል። የፖለቲካችን ችግር ሕዝብ የስልጣን ባለቤት እንዳይሆን ያገዱትን መሰናክሎችን የማስወገድ ችግር ነው። በአሁኑ ወቅት ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ይሁንታ ሳይሰጣቸው በጉልበትም ሆነ በሸፍጥ ስልጣን መያዝ አለብን ወይም ይቻላል ብለው የሚያሰቡ ድርጅቶች ቁጥራቸው እየተመናመነ ነው። ይህ ስሜት ያላቸው ድርጅቶች ቢኖሩም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ በአገር ውስጥና ከአገራችን ውጭ በማኅበረተሰባችን ውስጥ ዴሞክራሲን በሚመለከት የተደረሰበት ግንዛቤና ለዴሞክራሲ ትግሉ የተከፈለው መስዋዕትነተ የሚያነቃንቃቸው እንዳልሆነ ያውቁታል። አንዳቸውም በአደባባይ፣ ሕዝብ ፊት ቆመው ስልጣን በጉልበት ወይም ሕዝብን ባገለለ መልኩ በፖለቲካ ልሂቃኑ መካከል በሚደረስ የውስጥ ስምምነት መያዝ ይገባዋል ብለው መናገር ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ስልጣን ላይም ያለው አምባገነናዊ የወያኔ ድርጅት ሳይቀር ህጋዊነቱን ከዴሞክራሲ ጋር ለማያያዝ ሲተጣጠፍ እንጂ የስልጣኔ ምንጭ ከደደቢት በረሃ አንግቤ የመጣሁት ጠመንጃዬ ነው ብሎ ደፍሮ አይናገርም። ከእንግዲህ የዴሞክራሲን ጽንስ ሃሳብ የበላይነት በኢትዮጵያ ውስጥ ማንም ሊያስቆመው አይችልም።

ከዚህም በተጨማሪም ምርጫ 2002ን ተከትሎ የመጣው እውነታ የፖለቲካ ድርጅቶችን ሆነ የማኅበረሳባችን ግንዛቤ ቀይሮታል። ወያኔ ስልጣን ላይ እስካለ በምርጫ በሚደረግ የፖለቲካ ድርጅቶች ውድድር ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር እንደማይቻል ለሁሉም ግልጽ ሆኗል። ይህ እውነታ ቀደም ብለው በነበሩ የትብብር ሙከራዎች ተከስተው የነበሩ ችግሮችን አሰወግዷቸዋል። ወያኔ ስልጣን ላይ ሆኖ በምርጫ ስልጣን  መያዝ ይቻላል የሚል ቀቢጸ ተስፋ  በነበረበት ወቅት በድርጀቶች መሃል የሚደረግ ትብብር ተቃዋሚዎቹ ስልጣን ቢይዙ በሥራ ላይ ለማዋል በሚፈልጓቸው በርካታ ፖሊሲዎች ላይ የጋራ አቋም ይዘው መገኘት የግድ ይላቸው ነበር። ይህ ማለት የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ፣  አስተዳደራዊ፣ የውጭ ጉዳይና ሌሎችም ፖሊሲዎች ላይ የጋራ አቋም መያዝ ይገባቸው ነበር ማለት ነው። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጀቶች መካከል እንኳን በተጠቀሱት ፖሊሲዎች ዙሪያ ቀርቶ ከዛም ባነሱ ጉዳዮች ዙሪያ ስምምነት ላይ ደርሶ ትብብር መጀመርና የትብብሩን እድሜ ማራዘም ምን ያህል አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል በተግባር ያየነው ነው።

ምርጫ 2002  ያደረገው ነገር የፖለቲካ ድርጀቶችን ለስልጣን ከሚደረግው ትግል በፊት ፊታቸውን ስልጣን በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለመያዘ ወደሚቻልበት ትግል እንዲያዞሩ ማስገደድ ነው። በመሆኑም የፖለቲካ ድርጅቶች ቀደም ብለው በተጠቀሱት በበርካታ ፖሊሲዎች ዙሪያ ስምምነት ማድረግ ሳያስፈልጋቸው ለራሳቸውም ሆነ ለሕዘቡ የዴሞክራሲ መብቶች  እንዲረጋገጡ በጋራ ትግል ለማድረግ የሚችሉብትን ሁኔታ  ፈጥሯል። ከስልጣን መያዝ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ከትብብሩ ቀመር መወገዳቸው የመተባበር ሥራችንን አቅልሎታል።

ስልጣንን ለመጋራት የሚደረግ ትብብር እና ስልጣን በዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚያዝበትን ሁኔታ በጋራ ለማመቻቸት የሚደርግ ትብብር ለየቅል ናቸው። ስልጣን የሚያዘው በድርጅቶች መካከል በሚደረግ ድርድርና ትብብር ከሆነ “እኔ ስልጣን አነሰኝ፤ እከሌ ደግሞ በዝቶበታል” የሚል ጭቅጭቅ መቀስቀሱ አይቀሬ ነው። አንድ አይነት የትብብር ስምምነት ከተደረሰም በኋላም የሚገባኝን ስልጣን አላገኘሁም የሚል በሽታ ያገረሻል። ከፍተኛ ስልጣን በእጃቸው ይገባል ተብሎ  የሚታሰቡ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን መጠራጠር “ አድብተው ጉድ ሊሰሩን ይችላሉ” ብሎ  መስጋት ይኖራል። ይህ ጥርጣሬ በድርጅቶችና መሪዎች መካከል ያለውን መተማመን ገና ከመነሻው ያደፈርሳል።

ስልጣን የሚያዝበትን አግባብ ለማመቻቸት የሚደረገው ትብብር ግን ለእንዲህ ዓይነቱ ጥርጣሬ ሰፊ በር አይከፍትም። የ2002 የወያኔ የምርጫ መልክት “ስልጣን በምርጫና በዴሞክራሲ ስም ከወያኔ መውሰድ የሚቻለው በወያኔ መቃብር ላይ መሆኑን ግልጽ ማድረጉ ለስልጣን የሚደረግን ትብብር ከፈረሱ የቀደመ ጋሪ አድርጎታል።    ይህ እውነታ በማያጨቃጭቁ ጉዳዮች ዙሪያ እንድንተባበር መንገዱን ጠርጎልናል። ካለፉት የትብብር ውድቀቶቻችን ትምህርት መውሰድና  ለነበሩት ችግሮች መፍትሄ መስጠት እንችላለን የሚል ድፍረት የሰጠንም የሁኔታዎች መቀየር ነው። ምን ማድረግ ይቻላል?

## 5.2. በባህል ረገድ ያለብንን ችግር በሚመለት፣

ባህልን በአጭር ጊዜ መቀየር አይቻልም። የባህል ለውጥ ረጅም ሂደት ነው። ሆኖም ግን ያ የለውጥ ሂደት መጀመር ይኖርበታል፤ መጀመር ያለብንም እኛው ነን ። የሚከተሉትን ተግባራት በመከወን ረጅሙን የባህል ለውጥ አሁኑኑ መጀመር ይገባናል።

### 5.2.1. በድርጅቶች የሚሰራ፣

- ከባህላችን የሚቀዱ ባለፈው ተባብሮ ለመስራት የተደረጉ ሙከራዎችን ያደናቀፉ ችግሮችን በመለየት በድርጅቶች መካከል መኖር ስለሚገባው የግንኙነት ስነ-ምግባር ዝርዝር መመሪያ ደንብ ማዘጋጀት፤

- በዚህ መመሪያና ደንብ መሰረት ሁሉም ድርጅቶች እንደሚገዙ በሕዝብ ፊት ቃልኪዳን እንዲገቡ ማድረግ፤

- ከባህልና በሌሎችም ጉዳዮች የሚነሱ ችግሮችን የሚሸመግል የግልግል ቦርድ ማቋቋም። በሽምግልና (በግልግል) እልባት ባላገኙ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ ቦርድ ማቋቋም። በሚቋቋሙት ቦርዶች ውስጥ ሴቶችና ወጣቶች በቂ ውክልና እንዲኖራቸው ማድረግ። ቦርዶቹ ነጻና ገለልተኛ የፍትህ ተቋም በሚሰራበት መርህ እንዲደራጁና እንዲንቀሳቀሱ ማስቻል፤

- በዚህ ጉዳይ ላይ የተደረሰን የድርጅቶች ስምምነት ሁሉም ድርጅቶች ለአባላቶቻቸውና ለደጋፊዎቻቸው በሙሉ በእጃቸው በሚገኙ የመገናኛ አውታሮች ማስታወቃቸውን ማረጋገጥ፤

- በነፃ ሚድያዎች በጋራና በተናጠል በሚደረጉ ስብሰባዎች ይህንን የጋራ ስምምነት ለማኅብረተሰባችን ማሳወቅ፣

### 5.2.2. በነፃና ገለልተኛ ሚድያዎች የሚሰራ፣

- የድርጅት መሪዎችን፣ ባላሙያዎችን፣ ታዋቂ ግለሰቦችን እና ተቆርቋሪ ዜጎችን በማነጋገር የትብብሩ አድማስ እንዲሰፋ መጣር፤

- ሕዝባዊ የመገናኛ ብዙሃን የትብብር መድረኮችን አመቻች እንዲሆኑ ማበረታታት፤

- የትብብርን የስነ ምግባር ደንብ ሕዝብ በሚገባ እንዲያውቀው ማድረግ፤

- ይህንን ደንብ በመጣስ ችግር ፈጥረው፣ ራሳቸው ተስማምተው ያቆሟቸውም የሽምግልናና የውሳኔ ሰጪ ቦርዶችች ጥፋተኛ ያደረጓቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች ሕዝብ እንዲያውቃቸው ማድረግ፤

- የሽምግልና እና የውሳኔ ቦርዶችን ውሳኔ በሕዝብ እንዲታወቁ ማድረግ፣

## 5.3. በማኅበረሰባችን ውስጥ መሰራት የሚገባው፣

- ትብብርን የሚያደናቅፉ፣ ትብብሩ ውስጥ ከገቡ በኋላ ቃልኪዳን ያፈረሱ፤ ችግር መፍቻ ይሆናል ብለው ተስማምተው ያቆሙተን ተቋም ውሳኔ አልቀበልም ብለው የሚያፈንግጡ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ማግለል፤

- ከዚህ ቀደም እንደነበረው ጥፋተኛና ጥፋተኛ ያልሆነውን በይሉኝታና በአድርባይነት በእኩል ከሚስተናገዱበት ጎጂ ባህል ተላቆ ጥፋተኞች የሚወቀሱበት፤ በጎ የሰሩትን የሚያበረታቱበት ባህል እንዲዳብር መጣር፤

- የሲቪክ ማኅበራት ከገባንበት ሲኦል እንዳንወጣ የሚያደናቅፉንን ጎጂ ባህሪዎችንና ዝንባሌዎችን የመታገል፤ ዲሞክራሲያዊ ባህሎችን የመገንባት ግንባር ቀደም ኃላፊነት እንዲወስዱ ማበረታታት።

## 5.4. ሁሉንም ሊያስማሙ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ትብብር ማድረግ፣

- የአገራችን የፖለቲካ ሂደት ይህንን ችግር አቃሎታል። ሁሉንም የሚያስማማው የመተባበሪያ አጀንዳ አንድ ብቻ ነው። አሁን የትብብሩ ዓላማ የፖሊሲ አንድነት ለማምጣት ሳይሆን ሕዝብ እነዚህን የፖሊሲ ልዩነቶች በነፃነት አዳምጦ በነፃነት የሚበጀውን እንዲመርጥ ማስቻል ነው። የትብብሩን መሰረታዊ ዓላማ ይህንን በማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደፊት የምርጫ እድል አግኝቶ ውሳኔ በሚሰጥባቸው ጉዳዮች ላይ የፖለቲካ ድርጅቶች ትብብር አፍራሽ ወደሆነ አላስፈላጊ ንትርክ እንዳይገቡ ማድረግ ይቻላል።

- ሕዝብ ለፖለቲካ ድርጅቶች በነፃነት ድምጹን በመስጠት የስልጣንን ባለቤትነት እንዲወስን ለማድረግ በተደረሰ ስምምነት የሚጀመር መተባበር ለዚህ ዴሞክራሲያዊ ሂደት እንቅፋት የሆነውን ወያኔን ለማስወገድ ድርጅቶች የሚጠቀሙበት የትግል ስልት የመለያያ ነጥብ እንዳይሆን ማድረግ ይቻላል። ዓላማውን እንዲህ ግልጽ አድርጎ የሚነሳ ትብብር ሰላማዊና ህጋዊ፣ ሰላማዊ ግን ህጋዊ ያልሆነ፣ ሰላማዊና አመጽን ያካተተ ሁለገብ ትግል ወይም የአመጽ ትግል ብቻ እናደርጋለን በሚሉ ድርጅቶች መካከል እስካሁን የነበረውን ልዩነት አጥቦ ሁሉም በአንድ ላይ ተባብረው የሚታገሉበትን ሁኔታ ይፈጥራል።

- እነዚህን በጣም ቀላል የሆኑ የትብብሩን አላማዎች ሕዝብ በቀላሉ የሚረዳቸው ብቻ ሳይሆን በትብብር ውስጥ በርካታ ፖለቲካዊና ፖለቲካዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንዲሳተፉ የሚስቡም ናቸው። ከትብብር ለማፈንገጥ በር ስለማይከፍቱ ትብብሮች ግባቸውን እንዲመቱ የተሻለ እድል ይሰጣቸዋል።

## 6. ግቡን ሊመታ የሚችል ታላቅ የመተባበር እንቅስቃሴ እንዴት መጀመርና ማስተባበር እንችላለን?

### 6.1. እንደ መንደርደያ፣

ከተራ ቁጥር 5.2 እስከ 5.4 የተዘረዘሩት ተግባራት በሚገባ ከተፈፀሙ ከላይ ያቀረብነውን ጥያቄ የመመለሱ ሥራ ከግማሽ በላይ ተጠናቋል ማለት ይቻላል።

ከዚህ ቀጥሎ "ግቡን ሊመታ የሚችል ታላቅ የትብብር እንስቃሴ እንዴት ማስተባበር ይቻላል" በሚል የቀረበውን ግዙፍ ጥያቄ በተለያዩ ንኡስ ርዕሶች በመከፋፈል ለመመለስ እንሞክራለን። እነዚህን ጥያቄዎች በሙሉ በአግባቡ መመለስ ግቡን ሊመታ የሚችል ታላቅ የመተባበር እንቅስቃሴ ለመመስረት ወሳኝነት ይኖረዋል የሚል እምነት አለን። እነዚህ ጥያቄዎች "የመተባበሩን አጀንዳ በባለቤትነት ማን ያንሳው?" ከሚለው ተራ የሚመስል ጥያቄ አንስቶ የትብብሩን መነሻ፣ መሸጋገሪያና መድረሻ የሚመለከቱ ጥያቄዎችና ምላሾቻቸው በግልጽ የተካተቱባቸው ይሆናሉ። በእነዚህ ጥያቄዎች አማካይነት የትብብር ፍላጎታችንን ገና ከጅማሮው አንስቶ የመጨረሻው ምዕራፍ እስከሚደርስ ድረስ ሊያደናቅፉት ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ተግዳሮቶች በሙሉ አስቀድመን እናነሳለን። በእነዚህም የወገናችን የዘመናት የትብብር ጥማት የሚያረካና የአገራችንን ፍላጎት የሚያሟላ በምንም አይነት ማደናቀፊያና በማንኛውም ሁኔታ ውሉን የማይስት የትብብር እንቅስቃሴ ለመፍጠር እንችላለን ብለን እናምናለን።

### 6.2. ስለ መተባበር መነጋገር፣

እንደኛው በርካታ የፖለቲካና ፖለቲካዊ-ያልሆኑ ድርጀቶች "በአገራችን ጉዳይ ያገባኛል" ብለው በተነሱባቸውና ውለው አድረውም የተሳካ ትብብር ለማድረግ ከቻሉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ተመክሮዎች ለመማር እንደምንችለው ሌላው ቀርቶ ስለመተባበር ጉዳይ አንስተው ለመነጋገር የማይችሉባቸው ሁኔታዎች ገጥሟቸው እንደነበር ነው። በድርጅቶች ወይም በመሪዎች መካከል ያለው አለመግባባትና ጥርጣሬ አንዱ ለሚያደርገው ጥሪ ሌላው መልስ የማይሰጥበት ሁኔታዎች ይከሰታሉ። "ይህ ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚጠራው የመተባበር ስብሰባ አስቀድሞ ለራሱ ድርጅት እንደሚጠቅም ሆኖ የተዘጋጀ ነው" በሚል መነሻ ለጥሪው መልስ አለመስጠት የተለመደ ነው። አንዳንዴም የመተባበር ጥሪውን ያቀረበውን አካል ትንሽና ዝቅተኛ አድርጎ በማየት መልስ መስጠት "የድርጅትን ወይም የመሪውን ክብር ይነካል" በሚል ምላሽ የማይሰጥባቸው ሁኔታዎች ይኖራሉ። ሌላው በአደባባይ በአንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ ለሚጠራ የእንተባበር ጥሪ መልስ

መስጠት "ትብብርን ለመፍጠር መንሰፍሰፍን የሚያሳይ ምልክት ይሆናል፤ ይህም በድርድር ወቅት ይጎዳኛል" በሚል እምነት ለትብብር ጥሪ መልስ አይሰጥም።

በፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ሰፊ ልዩነት ያላቸው ቡድኖች በቀጥታ ስለትብብር መነጋገር ስለማይችሉ ንግግር እንዲጀመሩ አማላጅ እስከመላክ የሚያደርስ ፈተና ይገጥማል። ስለዚህም ነው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ኃይሎች ተገናኝተው ተባብረው እንዲሰሩ ለማድረግ ስለመተባበር የሚያደርጉትን የመጀመሪያ ስብሰባ ለመተራት ሳይቀር ብልህነት የሚጠይቅ ስራ ሊሆን ይገባዋል የምንለው። በዚህ ረገድ የሕዝባዊ ሚዲያ ተቋማት ሚና ከፍተኛ ነው።

እንደኛው በዚህ የመተባበር ጉዳይ ላይ ጨንቋቸው የነበሩ ማኅበረሰቦች ስለመነጋገር ለመነጋገር (talking about talks) ከሚል ዝቅተኛ ደረጃ የሚጀምር የውይይትና የድርድር ሂደት ማካሄድ የሚያስፈለግበት ወቅት እንደሚኖር የሚያስተምሩትም ለዚሁ ነው። ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው በመነሳት በሁላችንም ልብ ውስጥ የሚንቦገቦገውን የመተባበር ፍላጎት እንዴት እናስጀምረው? በበኩላችን መልሱ እነሆ።

- ዓላማችን ሁሉንም በአገራችን ጉዳይ ያገባኛል የሚሉ ኃይሎችን ያካተተ ኅብረት ለመፍጠር ከምር ዓልሞ መነሳት ነው። በኅብረተሰባችን ውስጥ ያለውን በጣም በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝና የተሰነጣጠረና ደካማ የሲቢቪክ ማኅበረሰብ የእድገት ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት ይህ የመተባበር ስራ በርካታ ትናንሽ ቡድኖችንም ማካተት እንደሚኖርበት መገንዘብ ተገቢ ይመስለናል።

- የድርጅቶቹ ትልቅነትና ትንሽነት፣ ያላቸው አደረጃጀት፣ የሚታገሉለት ዓላማ፣ የሚታገሉበት የትግል ስልት አንዱን ድርጅት አካቶ ሌላውን አግልሎ ለትብብር ውይይት ለመተራት በመስፈርትነት መቀመጥ አይኖርበትም። ማንኛውም ድርጅት የፈለገውን አቋም ይያዝ በጋራ ለመስራት ፍላጎት ማሳየቱ እንደ አንድ ትልቅ ድል ተደርጎ ሊወሰድ ይገባዋል። በዚህ ቀና ፍላጎት ላይ ቆሞ በቀና መንፈስ የሚደረግ ውይይት በሚያመጣው ውጤት ላይ ቅድመ-ብያኔ መስጠት ተገቢ እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልገናል።

- ይህ ማለት ሥራቸውን ፖለቲካ ያደረጉ በተወሰነ ደረጃ የተደራጁና በተወሰነ ደረጃም የፖለቲካ ኮንስቲትዮንሲ ያላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች በቅድሚያ ተቀራርበው እንዲሰሩና ለሚፈጠረው ትልቅና ሰፊ ትብብር የፀና መሠረት እንዲሆኑ ለማድረግ የተለየ ትኩረት ሊሰጠው አይገባም ማለት አይደለም። ልንፈጥር የምንፈልገው ትብብር ቀዳሚ ዓላማ የአገራችንን ፖለቲካ ሥርዓት ለማስያዝ ቢሆንም የተለያዩ ቡድኖችን ፍላጎቶችና ጥቅሞች ከማስከበር ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው። በመሆኑም ስለ ትብብር የሚደረገው የውይይት ጅማሮ የፖለቲካ ድርጅቶችን አቀራርቦ ንግግር እንዲጀምሩ ለማድረግ ለሚሰራው ሥራ የራሱን አስተዋጽኦ ማድረግ ይኖርበታል። በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ያለውን ልዩነት

አጥብቦ በጋራ እንዲሰሩ ማድረግ ከተቻለ ፖለቲካዊ ባልሆኑ በሲቪክ ድርጅቶች መካከል ሊጠብ የማይችል ምንም ልዩነት አይኖርም። ይህ ከሆነ በፖለቲካ ድርጅቶችና በሲቪክ ድርጅቶች መካከልም የሰፉ ቅራኔዎች ሊኖሩ እንደማይችል በድፍረት መናገር ይቻላል።

- በአገር ውስጥ ሆነ ከአገር ውጭ በሚገኘው ማኅበረሰብ መካከል ያለው ልዩነት በዋነኛነት የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችንና የድርጅቶችን አቋም በመደገፍ የተፈጠረ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። በሲቪክ ድርጅቶችም መካከል መተባበር መፈጠር ያልተቻለው አንዱ ሌላውን የሲቪክ ድርጅት የአንድ የፖለቲካ እምነት አራማጅና በስውር ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት ጋር ትስስር ይኖረዋል የሚል ጥርጣሬ በመኖሩ ነው። በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በፖለቲካ ፓርቲዎች መሃል መቀራረብ ሳይቻል በሲቪክ ድርጅቶች መካከል የሚደረግ መቀራረብና ትብብር ማስተባበር ፈጽሞ አይቻልም ባይባልም እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው። በፖለቲካ ርዕዮታቸው በኅብረተሰባችን ውስጥ የተለያዩ ኮንስቲቱየንሲዎ ችን ለመፍጠር የቻሉ የፖለቲካ ድርጅቶ ችን ማቀራረብና በጋራ እንዲሰሩ ማድረግ በማኅበረቡ ውስጥ ሊኖር የሚገባን ትብብር እንዲሳካ ማድረጊያው ቁልፍ መሳሪያ ነው።

- በአገራችን ጉዳይ ያገባቸዋል የሚባሉ ድርጀቶች ሁሉ ዝርዝር በማዘጋጀት አቅም በፈቀድ መንገድ ከእያንዳንዳቸው ጋር በተናጠልና በጋራ በመነጋገር ስለመተባበር ለመወያየት የሚደረግን ስብሰባ እንዴት እንጥራው በሚል ጉዳይ ላይ መመካከር ይኖርባቸዋል። ግለሰቦችና ድርጅቶች የሚያግባቧቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች እንዲያነጋግሩ የሥራ ክፍፍል በማድረግ ባጭር ግዜ ውስጥ የምክክሩን ምዕራፍ ማጠናቀቅ ይቻላል።

- በዚህ ድርድር ወቅት በልምዳቸውና በሙያቸው የሚጠቅሙ በኅብረተሰቡ ውስጥ ተደማጭነት ያላቸው የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችን ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉ ግለሰቦች ማካተት አስፈላጊ ይመስለናል። ወደ ፊት እንደምናየው እነዚህ ግለሰቦች ከምክር ለጋሽነት አልፈው ለሚተባበሩ ኃይሎች የሚጠቅሙ ሰነዶች አርቃቂና አዘጋጆች በመሆን ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል።

- በምክክሩ የተስማሙት ቡድኖችና ድርጅቶች በኤሌትሮኒክስ መሳሪያዎች በሚደረግ ኮንፈርንስ የትብብር ውይይት የሚያዘጋጅ አንድ ድርጅት ወይም ከተለያዩ ድርጅቶች የተውጣጣ አንድ ግብረ ኃይል ሰይመው የሥራን ዓይነትና የጊዜ ገደብ አስቀምጠው ለሚቀጥለው ምዕራፍ ራሳቸውን ማዘጋጀት ይችላሉ።

## 6.3. በተለያዩ ደረጃዎች የሚደረጉ ውይይቶችን ስለማድረግ፣

- ሁሌም ስለመተባበር የሚደረጉ ውይይቶችን ለመተባበር ምንም ችግር በሌላቸው ኃይሎች ማስጀመር ይቻላል። የሚፈለገው ሰፊ ልዩነት ያላቸውን አካላት ያቀራረበና ያካተተ ኅብረት

ከሆነ ግን ቅድሚያ ሊስጠው የሚገባው የትብብር ሥራ ልዩነት ያላቸውን ኃይሎች አቀራርቦ እንዲነጋገሩና እንዲስማሙ በማድረጉ ላይ ነው። ይህ ልዩነት ያላችውን ኃይሎች ሶስተኛ አካል በሚያደርገው ሽምግልና ወይም ተጽእኖ እንዲጀመር ማድረግ ይቻላል፤ ወይም ልዩነት አለን ከሚሉት አካላት መካከል አንዱ በተነሳሽነት ሌላውን በቀና መንፈስ በመቅረብ ውይይቱን ሊያስጀምረው ይችላል።

- ቀደም ብለን እንደጠቀስነው በማኅበረተሰባችን ውስጥ ያለው ልዩነት የሚዘወረው በፖለቲካ ድርጅቶቹ ዙሪያ ባሉ ልዩነቶች ስለሆነ በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል መኖር ለሚገባው የመተባበር ሥራ በቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይጠይቃል። እንዲህ ዓይነቱን የፖለቲካ ድርጅቶችን የማቀራረቡን ሥራ ሲቪክ ማኅበራት በተናጠል ወይም በጋር ሊያስጀምሩት ይችላሉ። ሆኖም ግን የሲቢክ ማኅበራት በጋራም ይሁን ወይም በተናጠል በአገራችን ሊፈጠር የሚገባውን የፖለቲከ ትብብር መሪዎች ወይም ማዕከሎች መሆን አይችሉም።

- ሁሉም ዓይነት ኃይሎች የሚገኙበትና የሚወያዩበት ስብሰባ ማድረግና ሁሉንም ጉዳይ ወቅቶና አበራይቶ ጉዳዩን መጨረስ የሚያዳዳ ሊሆን ይችላል። የማኅበረሰባችንን ባህልና ካለፉት የመተባበር ታሪካችን በመነሳት እንዲህ አይነቱ አካሄድ እንደማያዋጣ መረዳት ይኖርብናል። የመጨረሻው ግባችን ቀደም ብለን የጠቀስነውን ታላቅና ሁሉንም ለዴሞክራሲ የቆሙ ኃይሎች ትብብር ለመፍጠር ቢሆንም፥ ይህ ትብብር ለመፈጠር የሚደረግ ውይይት አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ጥቂት ቡድኖች መካከል ተጀምሮ እየሰፋና እያደገ መምጣት ይኖርበታል። እነዚህን አነስተኛ ቡድኖች የየድርጀቶቹን ተፈጥሮ፣ የትግል ስልት፣ የአደረጃጀት መርህ፣ የመንቀሳቀሻ ድባብ ወዘተ በመስፈርትነት በማስቀመጥ መቦደን ይገባል። የፖለቲካና ፖለቲካዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወያኔ ህጋዊና ህግ ወጥ አድርጎ የሚያያቸው፣ የትግል ስልታቸው የተለያዩ ድርጅቶች፣ በዲያስፖራ፣ በዲያስፖራና በአገር ቤት ፣ በአገር ቤት ብቻ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ፣ በግልጽና በህቡዕ የሚንቀሳቀሱ በሚል መመደብ ይቻላል:: ዞሮ ዞሮ ግን የማስተባበሩ ሥራ ሁሉም ኃይሎች ሊስማሙበት የሚገባ የጋራ ግብና የአጭር ግዜ ፕሮግራም ቀርጾ ሁሉንም በአንድ ሰፊ ትብብር ውስጥ በማካተት፣ ሁሉም በጋራ የተስማማበትን ዓላማ ግቡን እንዲመታ እንደ አንድ ኃይል ሆኖ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ነ ው።

## 6.4. ሁሉንም በጋራ የሚያስማማው የጋራ ግብ ምን ሊሆን ይችላል?

- ያለንበት ወቅት በታሪካችን ከመቼውም ግዜ የተሻለ ሁሉንም የዴሞክራሲ ኃይሎች ሊያስተባብር የሚችል ነው። ለዚህም ምክንያቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

- የወያኔ አዋራጅ የሆነ ዘረኛ አፈና ሁሉንም የአገሪቱን ሕዝብ አዳርሷል። ሌላው ሁሉ ቀርቶ መለስ ዜናዊ የሚገለገልበት ዘረኛነት መለስን ራሱንና ጥቂት የአፈናና የዘረፋ ጓዶቹን በስልጣን ላይ ለማኖር ታስቦ እንጂ መለስ በወርቅነቱ ከሚነግድበት የትግራይ ሕዝብ መሠረታዊ የመብትና የብልጽግና ህልም ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ገሃድ ሆኗል። ባጭሩ የወያኔ የማጭበርበሪያ ጭንብሎች በሙሉ ወልቀው ከአምባገነናዊ ገበናው ጋር ርቃኑን ቆሟል። የወያኔ የማጭበርበሪያ ስልቶች ተሟጠዋል። ከእንግዲህ የሚጭበረበርለት አገራዊ ሆነ የዓለም አቀፋዊ ማኅበረሰብ የለም።

- ይህ የወያኔ የአፈና ሥርዓት በተለይ የ2002 ምርጫ ብሎ ከከወነው በእብሪትና በንቀት ከተሞላ የትኛውም ቡድን ይህንን እኩይና በሃብትና በጉልበቱ የፈረጠመን ኃይል በተናጠል ታግሎ መብቱንና ጥቅሙን ማስከበር አስቸጋሪ እንደሆነ እንደማይችል ከምር እንዲረዳ አድርጎታል። ያለንበት ፈታኝ ወቅት የፖለቲካ ድርጅቶችንና የሲቪክ ማኅበራት ብቻ ሳይሆን፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ለጠባብ ድርጅታዊ ዓላማቸው ማስፈጸሚያ ሲሉ ተበታተኖና አቅሙ ተዳክሞ እንዲቀር ያደረጉትን የአገሪቱን ሕዝብ ኅብረት የሚጠይቅ መሆኑ ግልጽ ሆኗል። ይህ ግንዛቤ የቆየ ቢሆንም አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ ግን ደርሶ አያውቅም።

- የ2002 ምርጫ ህዝብ በ1997 ምርጫ በብዙ መስዋእትነት ሰለ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ምንነት የተማረውን ትምህርት ትክክለኛነት ዳግም አረጋግጦለታል። ስልጣን ከሃቀኛ የዲሞክራሲ ሂደት ውጭ በአዝጋሚም መንገድ ሆነ በአቋራጭ መያዝ እንደማይቻል ግልጽ አድርጎልናል። የምርጫ ሰነድ አዘጋጅቶ "ከሌላው ድርጅት በእነዚህ ፖሊሲዎቼ እለያለሁ ምረጡኝ" ለማለት ከመዘጋጀት በፊት የአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ጠንቅ የሆነውን ወያኔን ከስልጣን ማባረር ግዴታችን መሆኑ ግልጽ ሆኗል። ከዚህ ቀደም መሬት በግል ንብረትነት የሚያዘው በኢህአዴግ መቃብር ላይ እንዳለው ሁሉ ስልጣንም በምርጫ በዴሞክራሲ ስም ከወያኔ መውሰድ የሚቻለው በወያኔ መቃብር ላይ መሆኑን ግልጽ አድርጎልናል። **ትግሉ በወያኔ ቁጥጥር ስር በሆነ የምርጫ ቦርድ፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የፍትህ ሥርዓት፣ የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ኃይል ምርጫ ተካሂዶ እንዴት ስልጣን እንይዛለን ሳይሆን እነዚህ ተቋማት ነፃና ገለልተኛ ሆነው ተደራጅተው እንዴትስ ሁሉንም የሃገሪቱን ዜጎች በእኩልነት እንዲያገለግሉ ማድረግ ይቻላል የሚል ብቻ እንደሆነ የማያሻማ ሆኗል።**

- እነዚህ ምክንያቶች ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሲቪክ ማኅበራት እና የሃገሪቱ ሕዝብ በጋራ እውነተኛ የዴሞክራሲዊ ሥርዓት ግንባታ እንዲጀመር በቅድሚያ ተባብረው ሊሰሩት የሚገባ፣ በመካከላችው የሚኖሩ ማናቸውም ልዩነቶች፣ የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚ፣

የውጭ ጉዳይ የፖሊሲ ልዩነቶች በምንም አይነት ሊያደናቅፉት የማይገባ የጋራ ዓላማ ያላቸው መሆኑን አሳይተዋል። ይህ የጋራ ዓላማ አገራችን በአጭር የሽግግር ሂደት አልፋ ከአምባገነንነት በሕዝብ ነፃ ምርጫ ላይ ወደ ተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ መንግሥታዊ ሥርዓት መሸጋገር እንደሚኖርባት ነው። ለዚህም ሽግግር መሳካትና ተጠናክሮ መቀጠል የዴሞክራሲ ምርጫና መንግሥታዊ ሥርዓት ዋልታ የሆኑትን ነፃ ማኅበረሰባዊና መንግስታዊ ተቋማት መገንባት የሽግግሩ ወቅት ተቀዳሚ ሥራ መሆን እንደሚገባው ነው። ባለንበት ዘመን ከወያኔና የትግላቸው ዓላማ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰለሚመጣ ለውጥ ቁብ ከማይሰጡ ጥቂት ድርጅቶች በስተቀር ከዚህ በላይ በተቀመጠው ጥቅል የጋራ ዓላማ የማይስማማ አይኖርም። ከዚህ ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ ወደ ተባለው ግብ በጋራ ተነስተን እንዴት በጋራ እንደርሳለን የሚለው ብቻ ነው።

## 6.5. ከጋራ ፍላጎት ወደ ጋራ ዓላማ፤ ከጋራ ዓላማ ወደ ጋራ ትግልና ድል እንዴት?

6.5.1. ለጋራ ትግልና ድል መሠረት የሚጣለው በድርጅቶች መካከል ኅብረት ለመፍጠር የሚደረገውን በጥንቃቄ በመከነወን ሂደት ነው ። ከላይ በ 6.2 የቀረበውን ማሳሰቢያ በጥሞና ማጤን ጠቃሚ ነው።

6.5.2. በድርጅቶች መካከል በተደረጉ ውይይቶች የታየውን ተባብሮ የመሥራት ፍላጎት ዘላቂ እንዲሆን ለመሥራት ፍላጎቱ ያላቸው ድርጀቶች፣ ለራሳቸውም ሆነ በጉጉት ለሚጠብቃቸው ሕዝብ ከየት ተነስተው በምን አቋርጠው የት እንደሚደረሱ በግልጽና በያሻማ ቋንቋ የተቀመጠ የተሟላ እቅድ ( road map ) ሊኖራቸው ይገባል። ይህ የተሟላ እቅድ ድርጅቶቹ እርስ በርስ ቃል ኪዳን የሚገቡበት ብቻ ሳይሆን ለሕዝብም ጭምር ቃል የሚገቡበት መታሰሪያቸው ይሆናል። በዚህ እቅድ ውስጥ በሚካተቱ መሠረታዊ ነጥቦች ላይ አንድ ወጥ የጋራ ስምምንት ሳይደረስ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሆነ ወይም "ለጥቂት ጊዜ አብረን መስራት እስከቻልን ሌላውን ችግር ጊዜ ይፈታዋል" በሚል የሚደረግ ውለታና ስምምነተት ከቶወኑ ሊኖር አይገባም። በተውሸለሸለ መንገድ በሚፈጠር ትብብር የሕዝብ ቅስም በድጋሚ እንዲሰብር ልንፈቅድ አይገባም። በአገራችን ድርጅቶች መካከል የሚደረግ የስምምነት ውል የሚያፀናው <u>1) የድርጀቶችና የመሪዎቻቸው ቀና ፍላጎትና አርቆ አሳቢነት፤ 2) በተወሰን ደረጃም ቢሆን በሕዝብ ፊት የተገባ ቃል ኪዳንና ፤ 3) ውሉን በሂደት ለማፍረሰ ሰበብ ሊሆኑ ይቸላሉ ተብለው የሚታሰቡ ማናቸውም ችግሮቸ አስቀድሞ የታሰበባቸውና መፍትሄ የተሰጣቸው ከሆኑ ብቻ ነው።</u> በመሆኑም የተባለው እቅድ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነጥቦች ያካተተ ሊሆን የገባዋል።

1. ሁሉም ድርጀቶች የሚተባበሩበተን የጋራ ምክንያትና ግብ፣ በጋራ የሚጋሩዋቸውንና በምንም አይነት ሁኔታ የማይጥሷቸውን መሠረታዊ የጋራ እሴቶች የሚያሳይ ሰነድ፣

2. የጋራ ትግሉ የሚያልፍባቸውን ዋና ምዕራፎችና በየምዕራፉ የሚሠሩ ሥራዎችን በዝርዝር የሚያሳይ ሰነድ፣ ለምሳሌ

   - የትግል ምዕራፎቹ ምን እንደሚሆኑና በየምዕራፉ ስለሚከናወኑ ተግባራት፣

   - ወያኔ ከስልጣን ተወግዶ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሚሰይም መንግስት እስከሚሰየም ድረስ የሚኖረው የሽግግር ሂደት ምን ይመስላል? እንዴት ይዋቀራል፣ ምን ተግባራት ይኖሩታል?

   - ለዴሞክራሲ ሥርዓት ዋስትና ይሆናሉ ተብሎ የሚታሰቡትና በሽግግር ወቅት ይቋቋማሉ የተባሉት ተቋማት በተባባሪዎቹ ውልና ፍላጎት መሠረት እንዴት ነፃና ገለልተኛ ሆነው በሁሉም የትብብሩ አካላት ተቀባይነት እንዲያገኙ ተደርገው መዋቀር ይቻላሉ? የዚህ ሥራ ኃላፊ እንዲሆን ማንን በጋራ ተስማምተው ይሰይማሉ? ይህ አካል የሚሰጠውን ውሳኔ በጸጋ ለመቀበል አስቅድመው መስማማታቸውን የሚያሳዩ ስነዶችን ማን ያዘጋጃል፤ ማንስ ያስፈጽማቸዋል?

3. የጋራ ዓላማቸውን ለማሳካት ተባባሪዎቹ የሚጠቀሙበትንና ሥራን ስሉጥ በሆነ መንገድ የሚያሠራ የትብብሩ ድርጀታዊ መዋቅር ምን መሆን ይገባዋል? ትብብሩ ምን አይነትስ ህገ-ደንብ ይኖረዋል?

እነዚህና መሰል ጥያቄዎች ካሁኑ ምላሽ ይፈልጋሉ። እነዚህና ሌሎችም መሠረታዊ ስነዶች በዝርዝር ተዘጋጅተው የትብብሩ ስምምነት ወይም ውል አካል መሆን አለባቸው። በትብብሩ የጋራ ጉዞ የድርጅት ወይም የመሪዎች ጠባብ ፍላጎቶች ሊያደፈሩሱዋቸው ብሎም ትብብሩን ሊያመክኑ የሚችሉ መሠረታዊ ጉዳዮች በይደር መታለፍ አይኖርባቸውም። መሠረታዊ የሆኑ ሰነዶች አስቅድመው ገና የትብብሩ ውል በድርጅቶች መካከል ከመፈረሙ በፊት የሚጠናቀቁ በመሆናቸው፣ የሰጥቶ መቀበል የድርድር ውጤት እንጂ ድርጅቶች በመቧደን ወይም በትብብሩ ውስጥ በሚኖራቸው ወንበሮች ቁጥር የሚወሰኑ አይሆንም።

በመሆኑም የወደፊቱ ሥራ ይህ በሙሉ ስምምነት ተቀባይነት ያገኘን ዝርዝር እቅድ (road map) በተግባር ለመተርጎም ከሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውጭ ድርጀቶችን ሊያጨቃጭቁ የሚችሉ የውሳኔ ጉዳዮች አይኖሩም። ይህ አሠራር ድርጅቶች ብዙ ወንበር ስላላቸው ወይም በፖለቲካ ዓላማቸው ስለሚቀራረቡ አንዱ በሌላው ኪሳራ የሚፈልገውን በማስወሰን ችግር ይፈጥርብኛል የሚል ስጋትና ጥርጣሬን በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል። በትብብሩ የሥራ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ በመቀመጥ ሊገኝ የሚችልን ጠቀሜታ ስለሚያሳንሰው ከየድርጅቶቹ የሚነሳውን የስልጣን ሽኩቻ ይቀንሰዋል። የትብበሩ አካላት ቁጥር ቢበዛ የሚያሰበረግግ አይሆንም። እንዲያውም በርካታ ቡድኖች የትብብሩ አካል

P.O. Boxes: 4916, 2003EX, Haarlem, The Netherlands; 56281, London, N4 9BH, UK

እንዲሆኑ፣ ብዙሃኑን ያካተተ፣ ማናቸውም ፈተናዎች የማያኮላሹት ጠንካራ ትብብር እንዲኖር የሚያበረታታ ይሆናል።

በመጨረሻም በአገራችን እውነተኛ የዲሞክራሲ ሥርዓት እንዲመሰረት በጋራ ለመሥራት በሚደራደሩ ድርጅቶች መካከል የሚደረግ ድርድር በንግድ ባላንጣዎች መካከል የተፈጠረን ቅራኔ፣ ወይንም ኑዛዜ ባልተገኘለት ወራሾች መካከል የሚደረግ ድርድር ተደርጎ መታየት የለበትም። በእነዚህ ድርድሮች እያንዳንዱ አካል የተቻለውንና ያህል ተጠቃሚ የሚያደርገውን ድል ለመቀዳጀት ተግቶ ይሰራል። አንዱ ሌላው የሚፈልገውን እንዳያውቅ የመደራደሪያ ካርዶቹን ማንም እንዳያይበት ደረቱ ላይ ለጥፎ ይቀመጣል። አንዱ ሌላውን አካል የሚያቀርበውን መደራደሪያ በንፋግ መንፈስ ተሸፋፍኖ ያየዋል። በእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የተጠቀሱት አካላት በድርድር ችግራቸውን መፍታት ካልቻሉ ጉዳያቸው ወደ ህግና ዳኝነት ሄዶ መፍትሄ ያገኛል የሚል እምነት ስላላቸው በድርድር አንድ አይነት ስምምነት ላይ ካልደረሱ የድርድሩን መቋረጥ የሞትና የሽረት ጉዳይ አድርገው አያዩትም።

በአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የሚደረግ ድርድር ከላይ በጠቅስናቸው ምሳሌዎች መንፈስ ሊከናወን አይችልም። **<u>ድርድሩ ሁሉንም አሸናፊና ተጠቃሚ አድርጎ ሊያውጣ በሚችል መርህ ብቻ ነው ሊመራ የሚችለው</u>**። የድርድር ሂደት ቢደናቀፍ ከጋራ ውድመት በስተቀር በገላጋይ የሚተርፈን ጠቀሜታ አይኖርም። "ድርጅቴ ምን ያገኛል? እኔ ምን እጠቀማለሁ?" ከሚል ስሌት በላይ ተሻግሮ ሁላችንም "የዛች መከረኛ አገር ሕዝብ ምን ያገኛል? የመተባበሩ ሥራ እንዲሰምር ድርጅቶች እንዲቀራረቡ ድርጀታችን ምን ማዋጣት ይችላል?" በሚል ቀና መንፈስ የምንቀርበው ብቻ ነው መሆን የሚችለው። አንዳችን በሌላው ኪሳራ ትርፍ የምናገኝበትን ስሌት አስልተን ወደ ትብብር ምሥረታ የምንጠጋ ከሆነ እንኳን የትብብሩን ዒላማ ልንመታ ይቅርና ትብብሩም በእግሩ እንኳን ማቆም እንደማንችል መታወቅ ይኖርበታል።